# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

## የዘመነ ክረምት አምስተኛ ሰንበት

የቃሉ ትርጉሜ ስርወ ቃሉ ከርመ፣ ከረመ ካለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጓሜውም ወርኃ ዝናም፣ ወርኃ ነጐድጓድ፣ ዘመነ ባሕር፣ ዘመነ አፍላግ፣ ዘመነ ጠል፣ ዘመነ ደመና፣ ዘመነ መብረቅ ማለት ነው። የክረምት ዘመን ከሰኔ ፳፮ እስከ መስከረም ፳፭ ቀን ድረስ ነው።

## የዕለቱ ምስባክ

ዘያበቍል ሣዕረ ለእንስሳ
ወሐመልማል ለቅኔ ዕጓለ እመሕያው
ከመያወፅእ እክለ እምድር

እንጀራን ከምድር ያወጣ ዘንድ
ለምለሙን ለሰው ልጆች ጥቅም
ሣርንም ለእንስሳ ያበቅላል

መዝ ፩፻፫፤ ፲፬-፲፭

ወንጌል፥ ማቴ ፳፬፤፴፮-ፍጻሜ
ቅዳሴ፥ የኤጲፋንዮስ (ዐቢይ)

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

በቀዳሚ ገብሩ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድር
«በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ»

## በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ፪ኛ ቆሮ ፱፤፩-ፍጻሜ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፩ኛ ጴጥ ፫፤፲፰-ፍጻሜ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፳፯፤፳፩-፴፫ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

## የዕለቱ ትምህርት

### እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይና ምድርን ፈጠረ። ዘፍ ፩፤፩

ለዛሬ ትምህርት ርዕስ የመረጥነው የቅዱስ ያሬድ የመዝሙር ርዕስ ነው፤ ኃይለ ቃሉ ከኦሪት የተወሰደ ነው።

ትምህርቱ፥ ሁሉም ነገር ከመፈጠሩ በፊት እግዚአብሔር ነበረ፤ በብሉይ ኪዳን ታሪክ ውስጥ በመግቢያው ላይ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ የሚለውን ዐረፍተ ነገር ተጽፎ እናገኛለን። ይኸውም ጠለቅ ያለ ምስጢር ያለበት ከፍተኛ ትርጉም ያዘለ ነው።

አንደኛ፥ ያለንበት ዓለም የተፈጠረ መሆኑን ይናገራል፤ በዓይናችን የሚታዩት ሰማይና ምድር የተፈጠሩ ናቸው። ከመፈጠራቸውም በፊት አልነበሩም ማለት ነው።

ሁለተኛ፥ ፈጣሪያችን ማን እንደሆነ የሚገልጽልን ጥቅስ ነው፤ ፈጣሪም እግዚአብሔር ነው።

ሦስተኛ፥ ሰማይና ምድር በምን ጊዜ እንደተፈጠሩ ያስረዳናል፤ እግዚአብሔር በመጀመሪያ የፈጠረው ሰማይና ምድርን ነው። የመጀመሪያ ፍጥረቶቹ ናቸው። ከሰማይና ከምድር በፊት የፈጠረው ፍጥረት የለም። በሌላ አነጋገር የዓለም ታሪክ የተጀመረው በእግዚአብሔር ፈጣሪነት ነው፤ ዘመን ወይም ጊዜ የምንለው ነገር መጀመሪያው የፈጣሪ ሥራ ነው።

ሰማይና ምድር ሲባል፥ ሁሉንም ነገር ያጠቃልላል። በሰማይም ሆነ በምድር ያለው ሁሉ በእግዚአብሔር ተፈጥሮአል። ከዚህ ሌላ በመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ ዐረፍተ ነገር ሌላም ትምህርት እናገኛለን። ይኸውም ሁሉም ነገር ለመፈጠሩ በፊት እግዚአብሔር መኖሩን ነው።

ሰማይና ምድር ሳይፈጠሩ እግዚአብሔር አለ፤ ይኖራል የሚል ቃል ነው። እግዚአብሔር ለዘለዓለም ጀምሮ ያለና የሚኖር አምላክ በመሆኑ (መዝ ፺፤፪) እግዚአብሔር ከመቼ ጀምሮ ኖረ ብሎ ጥያቄ ማንሳት ተገቢ አይደለም።

እግዚአብሔር ሁሉን ነገር የፈጠረው በቃሉ ነው (ዕብ ፲፩፤፫ ። ዘፍ ፩፤፫ ። መዝ ፴፫፤፱ ። መዝ ፩፻፵፰) በቃሉ ፈጠረም ማለት እግዚአብሔር ዓለምን ሲፈጥር ሥራውን ከመጀመሩ አስቀድሞ የሚፈጥርበት አንዳች ግዙፍ መሣሪያ በእጁ አልነበረም ማለት ነው። በቃሉ ብቻ ሁሉን አድርጓአል። እግዚአብሔር ሁሉን የፈጠረው ታላቅ የሆነው ስሙ እንዲከብር ነው (መዝ ፰ ። መዝ ፲፰፤፩ ። መዝ ፩፻፵፰)።




EthiOrthodox e-mail Outreach **EthiOrthodox@AOL.COM**

## የእግዚአብሔር መጋቢነት

አንዳንድ ሰዎች ለተፈጠረው ነገር ሁሉ የራሱ የተፈጥሮ ሕግ ስለሚኖረውና ይህንንም ሕግ ተከትሎ ተፈጥሮ ስለሚኖር እግዚአብሔር ከቀን ወደ ቀን እንዲከታተለው አያስፈልገውም ይላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ የተፈጥሮ ሕግ መኖሩን አይክድም። ለምሣሌ ምድር ዘርን ለማብቀል የሚያስችላት የተፈጥሮ ሕግ አላት (ዘፍ ፩፥፲፩)። ለዘመናትም የተወሰነ ሕግ ስላለ መዝራትና ማጨድ፣ ብርድና ሙቀት፣ በጋና ክረምት፣ ቀንና ሌሊት ጊዜያቸውን እየጠበቁ መፈራረቃቸውን አያቋርጡም (ዘፍ ፰፥፳፪)። ከመውጣቱ ጊዜ ጀምሮ እስከ መጥለቂያው ድረስ ፀሐይ መንገዱን ያውቃል (መዝ ፲፱፥፭-፮)። ከዋክብትም ሕጋቸውን አውቀው አይለያዩም፤ ዘለላቸው እንደተጠበቀ ይኖራል። የሰባቱም ከዋክብት ዘለላ ለዓይን በማይታይ ማሰሪያ ታስሮ በጠፈር ላይ ሥፍራውን ይዟል። ኦሪዮን የሚባለው ኮከብ ቦታውን ያውቃል፤ ማዛሮት የተባሉትም ጊዜያቸውን ጠብቀው ይወጣሉ፤ ድብ የተባለውም ኮከብ ከልጆቹ ጋር እንደሌሎቹ የሰማይን ሥርዓትና ሕግ እየተከተለ ይኖራል (ኢዮ ፴፰፥፴፩-፴፫)። ሰባኪው እንደሚለው ፀሐይ ትወጣለች፣ ደግሞ ትገባለች፣ ነፋስ ወደ ደቡብ ይሄዳል፣ ወደ ሰሜንም ይዞራል። እንደ ወትሯቸው ፈሳሾች ሁሉ ወደ ባሕር ይሄዳሉ፤ ከፀሐይ በታች አዲስ ነገር የለም። ሁሉም እንደጥንቱ የራሱን ሕግ እየጠበቀ ይኖራል (መክ ፩፥፬-፲)።

የሥነ ፍጥረት ሕግ ራሱን የቻለ በራሱም የቆመ ሳይሆን ፈጣሪ አምላክ ያዘጋጀው ነገር ነውና ፍጥረታት ሁሉ እነዚህን ሕግጋት ጠብቀው የሚኖሩት እግዚአብሔር መሣሪያ አድርጎ ስለሚጠቀምባቸው ነው። ስለዚህ ለምሣሌ የበጋና የክረምት የመፈራረቅ ሕግ ቢኖርም የሚያፈራርቃቸው እግዚአብሔር ነው እንጂ አውቀው የሚያደርጉት ነገር አይደለም (መዝ ፻፬፥፲፱)። ቁጥር ሥፍር የሌላቸውን የከዋክብትን ሠራዊት በቁጥር የሚያወጣ እግዚአብሔር ነው (ኢሳ ፵፥፳፮)። ፀሐይና ጨረቃን ያዘጋጀ እርሱ ነው (መዝ ፻፬፥፮)። ለፀሐይ ቀንን ያስገዛው ለጨረቃና ለከዋክብትም ሌሊትን ያስገዛቸው ይህ አምላክ ነው።

ፍጥረታት ሕይወትን ያስገኙ ከእርሱ ነው፤ ዛፎችና ቡቃያዎች ፍሬ የማፍራት ኃይል ያገኙት ከተፈጥሮ ሕግ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ነው። ምክንያቱም ዘርን የምትሰጡ ፍሬ የምታፈሩም ሁኑ ብሎ ያዘዛቸው እርሱ ነውና (ዘፍ ፩፥፲፩-፲፪ ። ዘፍ ፩፥፳፱)። በምድር ላይ የበቀለው ነገር ሁሉ ለምልሞ የሚታየው እግዚአብሔር በየጊዜው ከሰማይ በሚሰጠው ዝናብ ስለሚያረካው ነው (ዘሌ ፳፮፥፬ ። ዘዳ ፲፩፥፲፬)። የፊተኛውና የኋለኛው ዝናብ በጊዜው የሚሰጥ ለመከር የተመደቡትንም ወራት የሚጠብቅ እግዚአብሔር ነው (ኤር ፭፥፳፬)። ስለሆነም የፊተኛውም ሆነ የኋለኛው ዝናብ ጊዜው ሲደርስ ሳይመጣ አይቀርም።

ነገር ግን ይህንን ሕግ ለዝናብ ወራት የወሰነው አምላክ ፈቃዱ ቢሆን ዝናብ እንዳይመጣ ሊከለክልም ይችላል። ለዚህም የኤልያስ ታሪክ በቂ ማስረጃ ሊሆን ይችላል። በዘመኑ አምልኮ ባዕድ ከመጠን በላይ በእስራኤል አገር ተስፋፍቶ ስለነበር የእግዚአብሔር ቁጣ ነደደና በሦስት ዓመት ውስጥ አገሩ በሙሉ ውኃ በማጣት እንዲሰቃይ አድርጎአል (፩ኛ ነገ ፲፯)። ከዓመት ወደ ዓመት ለዝናብ የተወሰኑትን ወራት እግዚአብሔር ሊለውጣቸው ይችላል ማለት ነው።

ሰዎች ሆኑ እንስሳት በተፈጥሮ መንገድ መውለዳቸው ይታወቃል። ብሉይ ኪዳን እንደሚያስተምረን መውለድም በእግዚአብሔር ኃይልና ሥራ የሚሆን ነገር ነው። ኢዮብ የሰው ልጅ በእናት ማህጸን ውስጥ መጸነሱ፤ ጽንሱም ሰው ሆኖ መወለዱን በታላቅ አድናቆት ሲያስበው በእግዚአብሔር ተኣምራዊ ሥራ የሆነ ነገር መሆኑን ስለተገነዘበ እንዲህ ይላል። በውኑ እንደ ወተት አላፈሰስኸኝምን? እንደ እርጎስ አላረጋኸኝምን? ቅርበትና ሥጋ አለበስኸኝ፤ በአጥንትና በጅማትም አጠነከርከኝ (ኢዮ ፲፥፲-፲፩)። በዚህ ቃል እንደሚገልጠው የወንድና የሴት የግብር ሥጋ መገናኘትም ሆነ የጽንሱ መጸነስ በእግዚአብሔር በፈጣሪነት ኃይሉ የሆነ ነገር ነው። መዝሙረኛው እግዚአብሔርን የሚያመሰግነው ተመሳሳይ በሆነ ቃል ነው። እንዲህ ይላል አቤቱ አንተ ኩላሊቴን ፈጥረሃልና በእናቴም ሆድ ሰውረኸኛልና። ግሩምና ድንቅ ሁኜ ተፈጥሬአለሁ አመስግናለሁ (መዝ ፩፻፴፱፤ ፲፫-፲፬)።

እንግዲህ ሰው የሚወለደው ለእናትና ለአባት የተፈጥሮ የመወለድ ችሎታ ያላቸው በመሆናቸው ነው ቢባልም ፈጣሪ እግዚአብሔር ነውና እያንዳንዱ ሰው የሚፈጠረው በእርሱ ተኣምራታዊ ሥራ ነው። በተፈጥሮ ኃይል ሳይሆን በእግዚአብሔር ኃይል መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል።

እንስሳትን አራዊትም ሕይወታቸውን የሚያገኙት በእግዚአብሔር ሥራ ነው። የበረሃ ፍየል የምትወልድበትን ጊዜ የሚያውቅ ዋሊያም በስንት ወራት ውስጥ እንደምትወልድና የምታምጥበት ጊዜ የሚመለከት እርሱ ነው። ወራትዋን የወሰነላት እግዚአብሔር ነው እንጂ ተፈጥሮ አይደለም (ኢዮ ፴፱፥፩-፬)።

ከዕለት ወደ ዕለትም ፍጥረቶችን ሁሉ የሚመግባቸው ወደ ሕይወት የጠራቸው አምላክ ነው። እግዚአብሔር ወደ ቆላዎች ከሚልካቸው ምንጮች በተራራዎችም መካከል የሚያልፍ ወቶች የዱር አራዊት የበረሃ አህያዎችም በመጠጣታቸው ጥማታቸውን ያረካሉ (መዝ ፩፻፬፥፩-፲፩)። የአንበሳ ግልገሎችን ለመንጠቅ ይጮኻል ከእግዚአብሔር ምግባቸውን ይሻሉ። ፀሐይ ስትወጣ ይሰበሰባሉ። በየዋሻቸውም ይተኛሉ፤ ሰውም ወደ ተግባሩ ይወጣል (መዝ ፩፻፬፥፳፩-፳፫)። ምግባቸውን በየጊዜው ትሰጣቸው ዘንድ እነዚህ ሁሉ አንተን ተስፋ ያደርጋሉ። በሰጠሃቸው ጊዜ ይሰበሰባሉ፤ እጅህን ትከፍታለህ፤ ከመልካም መጋቢ መሆኑን ተናግሮአል (መዝ ፻፬፥፳፯-፳፰)። በሕይወትም የሚኖሩት እርሱ በምድር ላይ እስኪያስቀምጣቸው ጊዜ ድረስ ብቻ ነው። ነፍሳቸውን በሚያወጣበት ቅጽበት ወዲያው ይሞታሉ ወደ አፈራቸውም ይመለሳሉ (መዝ ፩፻፬፥፳፱)። ከዚሁ መዝሙር በቁጥር ፴ መንፈስህን ትልካለህ፤ ይፈጠራሉም የምድርንም ፊት ታድሳለህ ተብሎ እንደተጻፈው የምድር ፍጥረታት በሞት እያለቁ ሲሄዱ በቦታቸው አዲሶች እንዲተኩ ያደርጋል። ሰውም እንስሳም በምድር ላይ መኖርን እንዲቀጥሉ ዘወትር አዲሶች ይወለዱ ዘንድ እግዚአብሔር የፈጣሪ ሥራውን የሚያቋርጥበት ጊዜ የለም።

ኢዮብ መከራ በጸናበት ጊዜ በማይገባ ከእግዚአብሔር ጋር ተከራክሮ ስለነበር በመጽሐፈ ኢዮብ ፴፰ እና ፴፱ እንምናየው ኢዮብ መልስ እንዲሰጥባቸው እግዚአብሔር አንዳንድ አስቸጋሪ ጥያቄ ያቀርብለታል። እነዚህም ጥያቄዎች እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሁሉ የሚጠብቅ አምላክ መሆኑን የሚገልጡ በመሆናቸው ጥበቡን፣ ማስተዋሉን፣ ኃይሉንም ታላቅ የሚያደርጉ ናቸው። ቀጥሎ ያሉትን እንመልከት።

በዋሾቻቸው ውስጥ ተጋድመው በጫካም ውስጥ አድብተው ሳሉ ለአንበሳይቱ አድን ታድናለህን? የልጆቿንስ ነፍስ ታጠግብ ዘንድ ትችላለህን? (ኢዮ ፴፰፥፴፱-፵)። ለእንስሳ አደን የሚያድን ኢዮብ አይደለም። ይህንን የሚያደርገው እግዚአብሔር ነው።

የዱር አራዊትን የሚመግብ የቁራ ልጆችም የሚበሉትን አጥተው ሲቅበዘበዙና ወደ እግዚአብሔር ሲጮሁ መብልን የሚሰጣቸው እርሱ ነው (ኢዮ ፴፰፥፵፩)። ለፈረስም ጉልበትን ይሰጣል (ኢዮ ፴፱፥፲፱)፤ ጭልፊት እንዛብቦ የሚታየው ወይም ክንፎቹን ዘርግቶ ወደ ደቡብ የሚበርረው ከኢዮብ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጥበብ የተነሳ ነው። ንስር ከፍ ብሎ ቤቱን በአርያም ማለት በከፍታ ቦታ ማድረግን በገደልም ላይ መኖርን እንዲሁም በገመገሙ፣ በጥጉም ማደርን የሚመርጠው ከእግዚአብሔር ተምሮ ነው። በመጽሐፈ ኢዮብ እንደተጻፈ በእግዚአብሔር ትእዛዝ የሆነ ነገር ነው (ኢዮ ፴፱፥፳፯-፳፰)።

ይህንን በመሰለ ጥበብ ሁሉ እግዚአብሔር ከዕለት ወደ ዕለት በእጁ የተፈጠሩትን ፍጥረታት ከብክቦ ይጠባቃቸዋል። ኢዮብም ይህንን ሁሉ ከሰማው በኋላ በታላቁ እግዚአብሔር ፊት ታናሽነት ተሰምቶት ከዚህ በፊት በተናገረው ነገር አፍሮ ዝም አለ። ጥፋቱንም በእግዚአብሔር ፊት እነሆ እኔ ወራዳ ሰው ነኝ የምመልስልህ ምንድር ነው? እጄን በአፌ ላይ እጭናለሁ። አንድ ጊዜ ተናገርሁ አልመልስም፤ ሁለተኛ ጊዜም ከእንግዲህ ወዲህም አልናገርም በማለት አመነ (ኢዮ ፵፥፬-፭)።

እግዚአብሔር አመዳዩን እንደ ባዘቶ ያሰጣል፤ ጉሙንም እንደ አመድ ይበትነዋል፤ በረዶውም እንደ ፍርፋሪ ያወርዳል። ከዚያም ቃሉን ልኮ ያቀልጠዋል (መዝ ፩፻፵፯፥፲፮-፲፰)። እርሱም የፈጠረው ፍጡር ሁሉ የተወሰነለትን ሥፍራና ጊዜ ስለሚያውቅ ፍጥረተ ዓለም በሙሉ ሥርዓት የተጠበቀ ነው። የሜዳ አህያ ከከተማ ውካታ መራቅን ይመርጣል፤ መኖሪያውም በረሃና የጨው ምድር መሆኑን ያውቃል (ኢዮ ፴፱፥፮-፯)። ወፎች በሊባኖስ ዝግባዎች ላይ ጎጆአቸውን ተራራዎች ላይ ተወስነው ይኖራሉ። እሽኮኮችም በድንጋዮች መካከል መኖርን ይወድዳሉ (መዝ ፩፻፬፥፲፯-፲፰)።

እግዚአብሔር ምድርን በፈጠረ ጊዜ በመጀመሪያ ጥልቅ በሆነ ውኃ የተከደነች ነበረች። የብስ ይገለጥ ዘንድ ግን ውኆች ይመለሱ ዘንድ አዘዛቸው። ከዚያ ወዲህም እግዚአብሔር ኃይለኛ የሆነውን ባሕር እንኳን ከተወሰነለት ድንበር አልፎ እንዳይሄድ ሲያዝዘው ይኖራል። ትልቁ ውቅያኖስ ሆነ በተራራዎች ላይ ቦታ ያገኙት ሐይቆች የተወሰነላቸውን ድንበር አልፈው ምድርን እንዳያጥለቀልቁ እግዚአብሔር ያግዳቸዋል (ዘፍ ፩፥፱-፲ ። መዝ ፬፥፮-፱)። እንግዲህ በምድር ላይ የሚኖሩት ሕዝቦች የጥፋት ውኃ ለሁለተኛ ጊዜ

# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

## እግዚአብሔር በመጀመሪያ ...

### የዘመነ ክረምት አምስተኛ ሰንበት


እግዚአብሔር ምድርን በፈጠረ ጊዜ በመጀመሪያ ጥልቅ በሆነ ውኃ የተከደነች ነበረች። የብስ ይገለጥ ዘንድ ግን ውኆች ይመለሱ ዘንድ አዘዛቸው። ከዚያ ወዲህም እግዚአብሔር ኃይለኛ የሆነውን ባሕር እንኳን ከተወሰነለት ድንበር አልፎ እንዳይሄድ ሲያዝዘው ይኖራል። ትልቁ ውቅያኖስ ሆነ በተራራዎች ላይ ቦታ ያገኙት ሐይቆች የተወሰነላቸውን ድንበር አልፈው ምድርን እንዳያጥለቀልቁ እግዚአብሔር ያግዳቸዋል (ዘፍ ፩፥፩-፪ ። መዝ ፬፥፮-፱)። እንግዲህ በምድር ላይ የሚኖሩት ሕዝቦች የጥፋት ውኃ ለሁለተኛ ጊዜ ቢመጣብንስ ምን እንሆናለን በሚለው ሃሳብ መጨነቅ አያስፈልጋቸውም። ምድር ለዘለዓለም እንዳትናወጥ በመሠረትዋ ላይ መሠርቷታል (መዝ ፩፻፬፥፭)።

ምድርና ውኆችም በእግዚአብሔር እጅ መሆናቸውን ለመግለጥ ሲል ኢዮብ ከዚህ ለየት ባለ አስደናቂ በሆነ ቃል እንዲህ ብሎ ተናግሮአል። ምድሪቱም በታችዋ አንዳች አልባ ያንጠለጥላታል ውኆችን በደመናዎች ያስራል ደመናይቱም ከታች አልተቀደደችም (ኢዮ ፴፰፥፲፩)።

መዝሙረኛው «ምድርን በመሠረትዋ መሠረታት» ይላል። ኢዮብም «በታችዋ አንዳች አልባ ያንጠለጥላታል» ብሏል። የመዝሙሩ አባባል ምሣሌ መሆኑ ይገባናል። ለምድር የተለያየ መሠረት ማለት ለምሣሌ አንድ ሕንጻ የተገነባበትን መሠረት የሚመስል ነገር እንደሌላት እናውቃለን። ስለዚህ በመሠረትዋ መሠረታት የሚለው ቃል ትርጉሙ ሌላ አይደለም፤ በእግዚአብሔር እጅ ተጠብቃ ለሰው የማትናወጥ ጥሩ መኖሪያ ሆናለች የሚል ይሆናል። ኢዮብ የተናገረው ቃል ግን ምሣሌ ሳይሆን በሕዋው ውስጥ ለምድር ያላትን አቀማመጥ በትክክል የሚገልጥ ነው ለማለት ይቻላል። እርሱ እንደሚለው በታችዋ አንዳች ነገር ሳይደግፋት ምድር ሥፍራዋን ይዛለች። ጨረቃና ፀሐይ ሌሎችም የጠፈር አካላት ሁሉ የሚያርፉበት ነገር ሳይኖራቸው እግዚአብሔር በታቻቸው አንዳች አልባ አንጠልጥሏቸው። ምድርም ልክ የዚህ ዓይነት ፍጥረት ናት።

በመሠረትዋ መሠረታት ወይም ደግሞ በታችዋ አንዳች አልባ አንጠለጠላት ቢባል የአባባል ልዩነት ብቻ እንጂ የትምህርት ልዩነት እንደማያመጣ ግልጽ ነው። ሁለቱ አባባሎች ተስማምተው ምድር ሁሉ ኃያል በሆነው በእግዚአብሔር እጅ የተጠበቀች መሆንዋን ያስረዳናል። በላይዋ ላይ የሚንቀሳቀሱትን ፍጥረቶች ሁሉ በሰላም ሊያኖር ሊከባከብም ይችላል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ... አሜን።



እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይና ምድርን ፈጠረ። ዘፍ ፩፥፩